# የሀዘን መግለጫ (ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ)

## *ከያ ትውልድ ተቋም*

***“መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ”*** ወደ ጢሞቴዎስ ምዕ. ፬ ቁ ፯



<<ያ ትውልድ ተቋም>> በታላቁ የቋንቋ ምሁር ሊቀ-ሊቃውንት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ዜና እረፍት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እንገልጻለን። የሀገር፣ የሕዝብ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የትውልድ፣ ተቆርቋሪው ምሁር ለዘላለም የማያባራ፣ ተዝቆ የማያልቅ ዕውቀት ሰጥተውን አልፈዋል። ተመራምራችሁ ድረሱበት ብለው የድርሻቸውን አበርክተዋል። እሳቸው የድካማቸውን ፍሬ፣ እውቀታቸውን ለሀገር፣ ለሕዝብ አውርሰዋል። ተረክቦ መጠቀም፣ ማለምለም የትውልድ ድርሻ ነው።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በርካታ ሥራዎችን ለውጭው ዓለምና ለሀገራችን በማስረከብ የኢትዮጵያዊነትን እምቅ ችሎታ ብቻ ሳይሆን ማንነታችንን ያሳዩ ምሁር ነበሩ። ከአበረከቱት ድንቅ ሥራዎች በነበር የሚታወሱ ሳይሆኑ እንዳሉ የሚጠቀሱ ህያው ሥራዎቻቸው ምስክር ናቸው። ሥራዎቻቸው ከትውልድ ትውልድ ለትምህርት፣ ለምርምር፣ ለጥናት፣ ይተላለፋሉና ሥማቸው አልፋ ኦሜጋ ነው።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ማን ናቸው? ምን ሠርተው ታወቁ፣ ምን አወረሱን? ውርሳቸውን እንዴት ትውልድ እናስተምርበት? ሌላም ሌላ ቀጣይ ጉዞዎች ስማቸውን ተጠቃሽ፣ ዕውቀታቸውን፣ ሥራዎቻቸውን ተፈላጊ ያደርገዋል። ደራሲያን፣ ጻሕፍት፣ ተመራማሪዎች ሁሌም ጌታቸው ኃይሌን ሲጠቅሱ የማይታይ ሕይወት ይሰጡዋቸዋል። ይህ የሥራ ውጤት ነው ከመቃብር በላይ ከፍ ብሎ ነፍስ የሚዘራላቸው። የምርምር ውጤቶቻቸው፣ የዕውቀት ኀተራዎቻቸው፣ የድምጽ ክምችቶቻቸው፣ የብዕር ከታቦቻቸው፣ በጥቅሉ ማንነታቸው እንደገና ይዳሰሳሉ፣ መጻሕፍቶቻቸው ዳግም ይነበባሉ፣ ሕይወታቸው እንደገና ህያው ይሆናል።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> የዛሬ ዘጠኝ ዓመት ሲመሠረት ትልቁን ድጋፍ ያደረጉት ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ነበሩ። ነፍሳቸውን ይማርና ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. (July 05, 2012) በያ ትውልድ ተቋም የምሥረታ በዓል ላይ ይህን መልዕክት አስተላልፈዋል፡-

*“እግዜር ይስጥልኝ። ያ ትውልድ የሚለው ድረ ገጽ መቋቋሙ ዘግይቷል። እንደውም ቀደም ብሎ የዛሬ አሥር፣ አሥራ አምስት ዓመት መውጣት ነበረበት። የሆነ ሆኖ አስባችሁ ይህንን ለማዘጋጀት በመቻላችሁ በጣም አስፈላጊ ነው ደስ ብሎኛል። ያ ትውልድ የሠራው ሥራ በድረ ገጽ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ አንድ ቀን ኢትዮጵያ ነጻ የወጣች እንደሆነ እንደውም መንገዶች ሁሉ በሱ ይሰየማሉ ብዬ አምናለሁ። ብዙ ሰዎች ያ ትውልድ የግራ ክንፍ ስለነበረ በዚያ ጊዜ ከነበሩት የግራ ክንፍ ጋራ በተለይም ከነህወሓት ጋራ ሊያገናኟችሁ ይፈልጋሉ። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት እንደ ሰማይና እንደ ምድር ነው። ህወሓት የተቋቋመው ወይንም የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር የተቋቋመው ትግራይን ነፃ ለማውጣት ነው። የኢትዮጵያ ያ ትውልድ ግን የተከተለው፤ ስህተት አለበት ቢባልም የአካሄድ ስህተት ነው እንጂ የኢትዮጵያን አንድነት ከጥያቄ ውስጥ የሚያገባ አልነበረም። በሁለቱም መሀልም ስምምነት ያልተገባው፣ ያልተገኘው በዚህ ምክንያት ነው። ውኃና ዘይት አብረው እንደማይስማሙ ወያኔዎችና የእኛ ትውልድ ልጆች በምንም ዓይነት የሚስማሙ አልነበሩም። አሁን እንግዲህ በእውነቱ ይህ ድረ ገጽ አምሮበታል፤ ወደፊትም እየተሻሻለ ይሄዳል። የብዙ መረጃ ምንጭ እንዲሆንም እንጥራለን ፣ ታሪክ መማሪያ ይሆነናል። ልጆቹንም እያንዳንዳቸውን የተቻለውን ያህል ፎቶ ግራፋቸውን ማስገባት፣ ስማቸውን መዘርዘር ገና ተጀመረ እንጂ አላለቀም። በዚያን ጊዜ ያለቁት ወጣቶች፣ ለሀገራቸው የሞቱት ወጣቶች እንደዚህ በአንድ ወር በሁለት ወር ውስጥ ተጠራቅም የሚያልቁ አይደሉም፤ ስማቸው ተጠራቅም የሚያልቅ አይደለም፤ የሚቀጥል ነው። ስማቸው መመዝገብ አለበት። ስማቸው የትም ወድቆ፣ ደማቸው የትም ፈሶ እንደቀረ ስማቸው ደግሞ የትም ወድቆ አይቀርም፤ መነሳት አለበት፤ ይሄ በመጀመሪያ ደረጃ የሚታይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ያ ትውልድ ትልቅ መታሰቢያ የሚሆነው የቆመለትን ዓላማ፣ ይዞት የነበረውን ችቦ ተቀብሎ ወደፊት የሚሮጥ ትውልድ መፍጠር ነው። የሱ ትልቁን ዓላማ ሐውልት የሚሆነው የቆመለትን ለኢትዮጵያ የቆመለትን ድካም፤ ኢትዮጵያ ነጻ ወጥታ እንዲታይ የሚያደርግ ሌላ ትውልድ እንዲፈጠር ነው። ሐውልት የሚሆነው ዓላማው ከግብ ሲደርስለት ነውና ይሄ እንዲሆን ደግሞ ሁላችንም በያለንበት መበርታት አለብን። እና በዚህ ላይ በርቱ እላችኋለሁ። መረጃ በምፈልግበት ጊዜ እንግዲህ ትልቁ ምንጭ እንዲሆነኝ ተስፋ አደርጋለሁ እና ስብሰባችሁንም እግዚአብሔር ይባርክላችሁ፣ ምርቃቱም የተባረከ ይሁንላችሁ። የኢትዮጵያ መታሰቢያ እንዲሆንላችሁ በሙሉ ልቤ እጸልያለሁ። አመሰግናለሁ።”* ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ።

«ያ ትውልድ ተቋም» በታላቁ ምሁር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ዜና ዕረፍት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እንገልጻለን። ለቤተሰቦቻቸው፣ ለዘመድ ወዳጆቻቸውና ለቅርብ ጓደኞቻቸው ብርታትና መጽናናትን ይስጥልን።
ነሲቡ ስብሐት <<ያ ትውልድ ተቋም>> ቦርድ ሰብሳቢ
ሰኔ 05 ቀን 2013 ዓ.ም. (June 12, 2021)
http://www.yatewlid.org/ , http://www.yatewlid.com/ ,email:- yatewlid@gmail.com ,Phone:- (703) 300 4302